# *CSO/NGOs' Taskforce for the Creation of an Enabling Environment for CSO/NGOs*

## *Comments Submitted to the Ministry of Justice (MoJ) on the Draft Charities and Societies Legislation*

***Addis Ababa***
***May 2008***

# በኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር በቀረበው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ረቂቅ አዋጅ ላይ ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቀረበ አስተያየት

(ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ/ም)

## ሀ. መግቢያ

በኢትዮጵያ በ1952 ከወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ እና ከ1959ኙ የማህበራት ምዝገባ ደንብ በስተቀር መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበረሰቡን ተቋማት እድገት፣ ፍላጎትና እንቅስቃሴ ያገናዘበ እና ዘርፉን የሚመለከት ሕግ ለረዥም ጊዜ ሳይወጣ ቆይቷል። ቀደም ሲል የወጣው ህግና ደንብ ጊዜ ያለፈበት እና ሲቪል ማኅበረሰቡ አሁን የሚገኝበትን ደረጃ ያላገናዘበ በመሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ምዝገባ፣ ቁጥጥር እና አስተዳደር በተመለከተ ቀደም ሲል በነበረው አሰራር በርካታ ችግሮች ታይተዋል።

የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለያየ ጊዜ -- ለምሳሌ በ1994፣ 1995 እና 1996 -- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ምዝገባና አሰራር የሚመለከቱ ረቂቅ አዋጆችን አሰራጭቶ ውይይት እንዲደረግባቸው አድርጓል ።

ሚኒስቴሩ ይህንን በጎ ጅምር በመቀጠል በቅርቡ በወጣው ረቂቅ የማኅበራት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ረቂቅ አዋጅ ላይ የኢትዮጵያን ሲቪል ማኅበረሰብ ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. በፍትሕ ሚኒስቴር አዳራሽ ጠርቶ አወያይቷል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለውይይት በቀረበው ረቂቅ አዋጅ እና በውይይቱ ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎች በቀረቡ ሀሳቦች ላይ የኢትዮጵያ መያዶች/የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ያላቸውን አስተያየት ለመንግስት ለማቅረብ ነው።

## ለ. ረቂቅ ህጉ መሰረት ያደረጋቸው ታሳቢዎች እና የፖሊሲ ምክንያቶች

የአዲሱን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ረቂቅ ዓላማ እና የፖሊሲ ምክንያቶች እንዲሁም ረቂቁ ታሳቢ ያደረጋቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስትር እና ከአርቃቂዎቹ መካከልም አቶ አባድር መሐመድ ሰፋ ያለ ገለጻ አድርገዋል። ከሕጉ የፖሊሲ ዓላማዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. በስራ ላይ ያለው ህግ ከወጣ ረዥም ጊዜ የሆነው እና በኢትዮጵያ ያለውን የሲቪል ማህበረሰብ እድገት፣ ባህሪያት እና እንቅስቃሴ ያላገናዘበ መሆኑ፤
2. የሲቪል ማህበረሰቡን ምዝገባ፣ አሰራር እና ቁጥጥር በሚመለከት በስራ ላይ ያለው ህግ እና አሰራር የተንዛዛ እና ለተጠያቂነት እና ክትትል የማያመች መሆኑ፤
3. የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የመንግስት የልማት አጋር የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ማስፈለጉ፤
4. በህገመንግስቱ የተረጋገጠውን የዜጎች የመደራጀት መብት በተግባር ላይ ለማዋል የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር፤
5. በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ውስጥ የሚፈጸሙ ህገ ወጥ ተግባራትን መለየትና አጥፊዎች ላይ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ህግ እንዲኖር ማድረግ።

የኢትዮጵያ መያዶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ከላይ የተዘረዘሩት ታሳቢዎች እና የፖሊሲ ምክንያቶች ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን እና በነዚህ ምክንያቶችም ቀደም ሲል የነበረው ህግ ሊሻሻል እንደሚገባ ያምናሉ። መንግስትም በዚህ ረገድ ያሳየውን ተነሳሽነት እና ጥረት ያደንቃሉ። በመሆኑም አዲስ የሚወጣው ህግ ለዜጎች የመደራጀት መብት የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥር፣ ተጠያቂነትን እና ግልጽነትን የሚያሰፍን፣ እንዲሁም ሲቪል ማህበረሰቡ ልማት እና ዲሞክራሲን በማጎልበት ረገድ የመንግስት አጋር እንዲሆን የሚያስችል ሊሆን እንደሚገባው የሲቪል ማህበረሰቡ ጽኑ እምነት ነው።

ይህን በማድረግ ረገድም የህጉ አላማ በቅድሚያ ለመያዶች/የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንቅስቃሴ የተመቻቸ ሁኔታ/enabling environment/ መፍጠር ሆኖ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ ረገድ በዋነኛነት ተቋማቱ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩበት እና ተጠያቂ የሚያደርጉበት ስርዓት/self-regulation/ ማመቻቸት ቢሆን የተሻለ ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም የመንግስት ድርሻ የተቋማቱን አቅም መገንባትና ማበረታታት፣ እንዲሁም አስፈላጊውን ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ሆኖ ህገወጥ ስራዎች ተሰርተው ሲገኙ የተቋማቱን ነጻነትና ህጋዊ አሰራርን በጠበቀ መልኩ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር ህጉ በተቋማቱ ነጻነት እና በተጠያቂነት መካከል ያለውን ሚዛን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ይህ ደግሞ በህገመንግስቱ እና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ህጉ ሊያሟላ የሚገባው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

ይሁንና በሚከተሉት ምክንያቶች ረቂቅ ህጉ አሁን ባለው ይዘቱ ከላይ የተዘረዘሩትን የፖሊሲ አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የማያስችል እና በተጠያቂነትና በቁጥጥር መካከል ያለውን ሚዛን ያልጠበቀ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከሌሎች ሀገሮች በጎ ተሞክሮዎች እንደታየው የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን የሚመለከት ህግ ከመውጣቱ በፊት በቅድሚያ ለተቋማቱ ነጻነት እና እንቅስቃሴ ምቹ የሆነ ማዕቀፍ ያካተተ እና በዚህ ረገድም የመንግስታዊ አካላትን እና የሲቪል ማህበረሰቡን ኃላፊነት በግልጽ የሚያመላክት፣ እንዲሁም ምዝገባ እና ቁጥጥርን በሚመለከት የሚወጣው ህግ ሊከተላቸው የሚገባውን የፖሊሲ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች የሚያስቀምጥ የሲቪል ማህበረሰብ ፖሊሲ መቅረጽ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ የፖሊሲ ሰነድ ህጉ ሊከተላቸው የሚገቡ አቅጣጫዎችን በግልጽ ያመላክታል፣ ህጉ ሊያሟላቸው የሚገቡ መመዘኛዎችንም ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም ሲቪል ማህበረሰቡን በሚመለከት የሚወጡ ህጎች በህገ መንግስቱና በአለም አቀፍ ስምምነቶች የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟሉ እንዲሆኑ የሚያስችል እና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እና በመንግስት መካከል ሊኖር የሚገባውን አጋርነት በተሻለ መንገድ የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከረቂቅ ህጉ በፊት የሲቪል ማህበረሰብ ፖሊሲ በመንግስት በኩል እንዲቀረጽ አበክረን እንጠይቃለን፡፡ ፖሊሲ የማርቀቁ ሂደትም መያዶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት በስፋት የሚሳተፉበት ሊሆን እንደሚገባ ጽኑ እምነታችን ነው፡፡

2. በመያዶች እና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ውስጥ ተጠያቂነትን ማስፈን የሚቻለው በዋነኛነት በመንግስታዊ ቁጥጥር ብቻ ሳይሆን በተቋማቱ ራሳቸውን በራሳቸው የመቆጣጠሪያ ስርዓት/internal systems of control and accountability/ አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተቋማቱ ያሏቸው መዋቅሮች -- ለምሳሌ ጠቅላላ ጉባዔው፣ ቦርዱ እና ሌሎችም አካላት ተገቢው የቁጥጥር ስልጣን እንዲኖራቸው በማድረግ እንዲሁም ውስጣዊ የአሰራር ደንቦቻቸው ግልጽነትና ተጠያቂነትን እንዲያሰፍኑ የሚያስችሉ መመዘኛዎች /minimium standards/ በማስቀመጥ እና እነዚህም መሟላታቸውን በመቆጣጠር፣ ተጥሰው ሲገኙም ተመጣጣኝ እና ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ነው፡፡ ይሁንና ረቂቅ ህጉ ይህንን በማድረግ ፈንታ ተጠያቂነትን ለኤጀንሲው ሰፊ የቁጥጥር እና የቅጣት ስልጣን በመስጠት ለማረጋገጥ መሞከሩ የተቋማቱን የአሰራር ነጻነት የሚጥስ ከመሆኑም በላይ ተገቢ ላልሆነ አሰራር /abuse/የተጋለጠ አድርጎታል፡፡

3. በሲቪል ማህበበረሰብ ተቋማት/መያዶች ምዝገባ እና ቁጥጥር ላይ የሚታዩት በርካታዎቹ ድክመቶች የመነጩት ከማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት አሰራር እና ከተቋማዊ አቅም ማነስ ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ ሊከናወን ይገባ የነበረው ተግባር የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት በስራ ላይ ያለውን ህግ ተጠቅሞ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር እንዳያደርግ እንቅፋት የሆኑትን አሰራሮች ለይቶ የማውጣት እና መፍትሔ የመስጠት፣ እንዲሁም ተቋማዊ አሰራሩንና አቅሙን መገንባት መሆን ነበረበት፡፡ ይህ ከተደረገ በኋላ በህጉ ረገድ ያሉ ክፍተቶች ተለይተው የተቋማቱን የውስጥ ነጻነት እና የዜጎችን የመደራጀት መብት በማይገድብ መልኩ የህግ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይገባ ነበር፡፡ ይህ ባለመደረጉ እና የአሰራር ችግሮችን በህግ ለመቅረፍ በመሞከሩ ረቂቅ ህጉ ኤጀንሲው በተቋማት የውስጥ አስራር በስፋት ጣልቃ ለመግባት የሚያስችለው ስልጣን እንዲሰጠው እና የተቋማቱ ህልውና እና የውስጥ አሰራር ነጻነትን የሚገድብ ሆኗል፡፡

4. በኢትዮጵያ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን/መያዶችን በሚመለከት የሚወጡ ህጎች ከህገ መንግስቱ በተጨማሪ በተቻለ መጠን ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እና የመግባቢያ ሰነዶች፣ እንዲሁም መንግስት ካወጣቸው የልማትና ዲሞክራሲ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ ረቂቅ ህጉ ኢትዮጵያ

ፈራሚ በሆነችባቸው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች፤ የኮቶኑዉ ስምምነት /Cotonou Agreement/፣ የአፍሪካ ህብረት ማቋቋሚያ ስምምነት፣ የኔፓድ እና ኤፒአር ኤም ሰነዶች /NEPAD and APRM documents/ እና ሌሎችም ስምምነቶች ፣ እንዲሁም PASDEPንና የኢች አይ ቪ ፖሊሲውን ጨምሮ መንግስት ባወጣቸው የድህነት ቅነሳ እና ልማት ፖሊሲ ሰነዶች መሠረት መንግስት የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ሚና በማጎልበት እና ለእንቅስቃሴያቸው የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ ያለበትን ኃላፊነት እና ሊጫወት የሚገባውን ሚና ከግምት ውስጥ በሚያስገባ መልኩ እንደገና ቢታይ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለን፡፡

በተጨማሪም ረቂቅ ህጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እስካሁን በልማት፣ በድህነት ቅነሳ እና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ረገድ የመንግስት አጋር በመሆን ያከናወኗቸውን በርካታ ጠቃሚ ስራዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ለወደፊቱ በተሻለ በአጋርነት እና የትብብር መንፈስ ተቋማቱ በልማት እና በመልካም አስተዳደር ረገድ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያበረታታ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ ረቂቅ ህጉ ያሉት ጠንካራ ጎኖች እንደተጠበቁ ሆነው መያዶች/የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን እድገት የሚያቀጭጩ እና በልማት እና በመልካም አስተዳደር ረገድ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ የሚገድቡ አንቀጾች ያሉት በመሆኑ እነዚህ አንቀጾች በዚህ ጽሑፍ እንደተመለከተው ተገቢው መሻሻል ሊደረግባቸው እንደሚገባ ይታመናል፡፡

## ሐ. በረቂቅ አዋጁ ላይ የቀረበ አጠቃላይ አስተያየት

### 1. የውይይት ሒደቱን በተመለከተ

በረቂቅ ህጉ ላይ በፍትህ ሚኒስቴር የተዘጋጀው ውይይት የተካሔደው ረቂቅ ህጉ ለመያዶች ከደረሳቸው ከ3 ቀን በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም መያዶች/ሲቪል ማህበራት ከረቂቅ ህጉ ስፋት እና ከህጉ አዲስነት እንዲሁም ውስብስብነት አንጻር በጥልቀት ጉዳዩን ለመመርመር እና ባለሙያ አማክሮ አስተያየት ለመስጠት የነበረን ጊዜ በጣም አጭር ነበር፡፡ አስተያየታችንን በጽሑፍ እንድናቀርብ ዕድል ስለተሰጠን ከፍተኛ ምስጋና የምናቀርብ ቢሆንም አሁንም ከተሰጠን አጭር ጊዜ አንጻር ሰፊውን የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ በረቂቅ ህጉ ላይ በቅጡ ለማወያየትና አስተያየቱንም በተሟላ ሁኔታ ለማካተት አለመቻላችንን መግለጽ እንወዳለን፡፡ ስለሆነም

- ረቂቅ ህጉ ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሲቪል ማህበረሰብ አባላት በስፋት ማወያየት ከዲሞክራሲያዊ አሰራር እና አሳታፊነት መርህ አንጻር አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ቀደም ሲል የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር መያዶችን በሚመለከት ባወጣቸው ረቂቅ ህጎች ላይ ሰፊ እና ተከታታይነት ያላቸው ውይይቶች በሲቪል ማህበረቡ መካከል እና በመንግስት እና በሲቪል ማህበረሰቡ ተወካዮች መካከል መካሔዳቸውን በማስታወስ አሁንም ይህ በጎ ልምድ እንዲቀጥል ለማስቻል፣
- በቅርቡ የፕሬስ እና መረጃ ነጻነት አዋጅ ረቂቅ ላይ በሚዲያው ማህበረሰብ እና በመንግስት መካከል የነበረው ሰፊ እና ጥልቀት ያለው ውይይት የማድረግ ዕድል ለሲቪል ማህበረሰቡም ሊሰጠው የሚገባ በመሆኑ፣
- ረቂቅ ህጉ መሠረት ካደረጋቸው እና በጎ ተሞክሮ ካላቸው እነ ደቡብ አፍሪካን በመሳሰሉ ሀገሮች ተመሳሳይ ረቂቅ ህጎች ብቻ ሳይሆኑ ማሻሻያዎችም ጭምር ሰፊ ውይይት እንዲደረግባቸው በህግ መደንገጉን እና ይህንንም እንደ በጎ ልምድ ልንከተለው የሚገባ መሆኑን በማስታወስ፣

ረቂቅ ህጉ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ከመቅረቡ በፊት ተከታታይነት ያላቸው ውይይቶች በሲቪል ማህበረሰቡ መካከል ለማካሔድ የሚያስችል በቂ ጊዜ እንዲሰጠን እንዲሁም ከዚህ ቀደም ይደረግ እንደነበረው በህጉ አርቃቂዎች እና በሲቪል ማህበረሰቡ ተወካዮች መካከል በዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ ተከታታይነት ያላቸው ውይይቶች የሚደረጉበት ሁኔታ እንዲመቻችልን በአጽንኦት እንጠይቃለን፡፡

### 2. የረቂቅ ህጉ ጠንካራ ጎኖች

የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት/መያዶች በረቂቅ ህጉ አንዳንድ አንቀጾች ላይ ያሉን ስጋቶች እንደተጠበቁ ሆነው ረቂቅ ህጉ በርካታ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ይገነዘባሉ፤ ለዚህም ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ ጠንካራ ጎኖች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

ሀ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን /መያዶችን በተመለከተ ራሱን የቻለ ህግ እንዲወጣ መደረጉ፤ ከላይ በመግቢያው እንደተጠቀሰው በስራ ላይ ያሉት ህጎች ማህበራትን እና በጎ አድራጎትና መሰል ድርጅቶችን በሚመለከት ከተቀመጡ አጠቃላይ ድንጋጌዎች በስተቀር የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን እንቅስቃሴ፤ አሰራር እና ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ የተቀረጹ ባለመሆናቸው ለተቋማቱ እንቅስቃሴ የተመቻቸ ሁኔታ አልነበረም። መንግስት የመያዶችን/ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ባህሪያት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ራሱን የቻለ ህግ እንዲቀረጽ ማድረጉ ወቅታዊ እና የሲቪል ማህበረሰቡም ለረዥም ጊዜ ሲጠብቀው የነበረ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚታየው ሌላው አዎንታዊ እርምጃ የማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ምዝገባና ቁጥጥር ለማከናወን ራሱን የቻለ ኤጀንሲ እንዲኖር መደረጉ እንዲሁም የማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚመለከት ምክር ቤት መቋቋሙ ነው። በዚህ ረገድ ማህበራት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች እንደ ባለድርሻ አካላት ዕውቅና ኖሯቸው በምክር ቤቱ ውስጥ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው በቂ ተወካዮች እንዲኖሯቸው እና ምክር ቤቱም የኤጀንሲውን ስራ የሚቆጣጠርበት እና ከማህበራትና በአድ የሚመጡ ቅሬታዎችን የሚያስተናግድበት ስርዓት በአዋጁ ቢካተት የተሻለ ይሆናል።

ለ/ ማህበራት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን በሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌዎች መውጣታቸው፤ በረቂቅ ህጉ መያዶች/ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ያሏቸውን ባህሪዎች ባገናዘበ መልኩ ማህበር እና የበጎ አድራጎት ድርጅት /በአድ/ በሚል ተከፍለው ለሁለቱም አይነት ድርጅቶች ዝርዝር ድንጋጌዎች ወጥተዋል። ይህ በጎ እርምጃ የሚደገፍ ነው። ይሁንና በኢትዮጵያ የሚገኙት አብዛኞዎቹ ሀገር በቀል ማህበራትና ድርጅቶች በረቂቅ ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት በበጎ አድራጎት ማህበርነት የሚፈረጁ ሆነው ሳለ በረቂቁ በጎ አድራጎት ማህበራትን በሚመለከት ያለው አንድ አንቀጽ /አንቀጽ 50/ ብቻ ነው። በተጨማሪም አንቀጽ 50/2/ ማህበራት እና በአድን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በበጎ አድራጎት ማህበራት ላይ ይፈጸማሉ ስለሚል በአንድ ጉዳይ ላይ ለማህበራትና ለበአድ የተለያዩ ድንጋጌዎች ሲኖሩ /ለምሳሌ ከገቢ ግብር ነጻ ስለመሆን/ በበጎ አድራጎት ማህበራት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የትኞቹ ድንጋጌዎች እንደሆኑ ግልጽ አይደለም። በተቃራኒው አዋጁ በኢትዮጵያ በብዛት ለማይገኙት የበጎ አድራጎት ተቋም የዘለቄታ በአድ እና የአደራ በአድ ዝርዝር ድንጋጌዎች አካትቶ ይታያል። ስለሆነም በአድን የሚመለከተው ክፍል በዋናነት በበጉ አድራጎት ማህበራት ላይ በማተኮር ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲኖሩት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።

በተለይ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን በሚመለከት በአንቀጽ 16/3/ የተዘረዘሩት አላማዎች በአሁኑ ጊዜ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች/መያዶች የሚገኙበትን ደረጃ ያገናዘቡ እና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ከሞላ ጎደል በዝርዝር ያካተቱ ሆነው አግኝተናቸዋል። በተጨማሪም መያዶች የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመለወጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ በግልጽ ቢካተቱ አንቀፁን ይበልጥ የተሟላ ያደርገዋል።

በመጨረሻም ለበአድ እና ለማህበራት እንደተደረገው ሁሉ በውጭ ሀገር የተቋቋሙ ማህበራትን ምዝገባ ፈቃድ አሰጣጥ እና አሰራር የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በአዋጁ በአንድ ክፍል ተለይተው ቢገኙ አዋጁ የተሻለ ግልጽ እና ለአፈጻጸም የቀለለ ይሆናል።

ሐ/ የበአድ ወይም ማህበራት ጥምረት መመሥረት እንደሚቻል መገለጹ፤ በስራ ላይ ባሉት ህጎች ከታዩት ችግሮች አንዱ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህብረት ህጋዊ መሠረት የሚሰጥ ድንጋጌ አለመኖሩ ነበር። በዚህ ረገድ በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 6/1/ ማህበራት ስራቸውን የሚያስተባብር ህብረት ማቋቋም እንደሚችሉ መገለጹ ረቂቁ ካሉት በጎ ጎኖች ዋነኛው ነው። ይህ በጎ እርምጃ የተሟላ እንዲሆን ማህበራትና በአድ ስራቸውን ለማስተባበር ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ህጋዊ አላማ /ለምሳሌ የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ወይም የጋራ አላማ ለማራመድ/ ህብረት የሚቋቋም መብታቸው በህጉ ቢታወቅላቸው የተሻለ ይሆናል።

መ/ በአድ እና ማኅበራት የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ መፈቀዱ፤ ይህ እርምጃ ማህበራት እና በአድ በሀገር ውስጥ ያላቸውን አቅም ይበልጥ እንዲገነቡ እና ስራዎቻቸውም ዘላቂነት እንዲኖራቸው የሚያስችል በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ የምንደግፈው ነው።

ሠ/ በአድ ከገቢ ግብር ነፃ እንዲሆኑ መደረጉ፤ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከገቢ ግብር ነጻ መደረጋቸው ለህዝብ የሚሰጡትን አገልግሎት ያገናዘበ እና የተሻለ የገንዘብ አቅም እንዲኖራቸው የሚያስችል

መልካም እርምጃ ነው፡፡ ይህ በጎ እርምጃ የተሟላ እንዲሆን ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑት ማህበራትም ከገቢ ግብር ነጻ እንዲሆኑ ቢደረግ የተሻለ ነው፡፡ በተጨማሪም ማህበራት እና በአድ ከተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ነጻ ቢደረጉ እና አስካሁን እንደሚደረገው ከውጭ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች ከቀረጥ ነጻ ቢሆኑ በዚህ ረገድ ያለው ድጋፍ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል፡፡

## 3. በረቂቅ ህጉ ሊታሰብባቸው/ሊሻሻሉ የሚገቡ ጉዳዮች

### 3.1. የረቂቅ ህጉን መግቢያ በተመለከተ

የረቂቅ ህጉ መግቢያ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የመንግስት የልማት እና ዲሞክራሲ አጋር መሆናቸውን በሚያረጋግጥ እና በዚህ ረገድ ከዚህ ቀደም ላበረከቱት ገንቢ አስተዋጽኦ ዕውቅና በሚሰጥ መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአዋጁ ዋና አላማ ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እንቅስቃሴ የተመቻቸ ህጋዊ ማዕቀፍ መፍጠር መሆኑ መገለጽ አለበት ብለን እናምናለን፡፡ በተለይ የመግቢያው 3ኛ አንቀጽ ሲቪል ማህበረሰቡን አሉታዊ በሆነ መልክ ማቅረቡ ተገቢ ካለመሆኑም በላይ የአዋጁ ዋና አላማ ቅጣትና ቁጥጥር እንደሆነ ያስመስላል፡፡ ስለሆነም ይህ አንቀጽ የአዋጁ አላማ ሲቪል ማህበረሰቡ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠርበት የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓት መገንባት መሆኑን በሚገልጽ አንቀጽ ሊተካ ይገባል፡፡

### 3.2. የመያዶችን/ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ዜግነት በተመለከተ (አንቀጽ 2(3))

የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 2(3) በኢትዮጵያውያን የተመሠረቱ እና በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተቋቋሙ ማህበራት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ከ10% በላይ የሚሆነውን ገቢያቸውን ከውጭ በማግኘታቸው ብቻ እንደውጭ ሀገር ድርጅቶች እንደሚቆጠሩ ይደነግጋል፡፡ ይህ አንቀጽ

- ከ10 በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ እርዳታ በማግኘት በልማት እና በዲሞክራሲ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉትን እና በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን ሀገር በቀል ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ እና ህገመንግስታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት የሚጥስ በመሆኑ፤
- የተቋማቱ የገቢ ምንጭ ከዜጎች የመደራጀት መብት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው በመሆኑ፤
- ከአንቀጽ 16(6) ጋር ተጣምሮ ሲነበብ አብዛኞቹ ሀገር በቀል ድርጅቶች በልማት ፖሊሲ ተሟጋችነት፣ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ፣ በዲሞክራሲ ግንባታ፣ እና ግጭቶችን በመፍታት እንዲሁም በዜግነት እና ማህበረሰባዊ ልማት ስራዎች በጥቅሉ በፖሊሲ እና መልካም አስተዳደር ስራዎች የሚያደርጉትን ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያቆሙ የሚያስገድድ ስለሆነ እና ይህም በሀገሪቱ በመገንባት ላይ ያለውን ዲሞክራሲ እና ልማት በእጅጉ የሚጎዳው ከመሆኑም በላይ የተጠ ቃሚዎች መብትን ስለሚጻረር፤

- አንቀፁ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰቡን እድገት (እለታዊ እርዳታ ከማቅረብ ወደ ማህበራዊ አገልግሎት፣ ከዚያም መብት ተኮር ወደሆነ የልማት እንቅስቃሴ እና ተሟጋችነት) ወደኂላ በመቀልበስ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ለልማት እና ዲሞክራሲ መጎልበት ወሳኝ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ተቆጥበው በእርዳታ እና አገልግሎት አቅርቦት ላይ ብቻ እንዲወሰኑ የሚያደርግ አሉታዊ ውጤት ያለው በመሆኑ ፤

- ከአንቀጽ 74(1) (ሠ) ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ከገቢያቸው 10% በላይ ከውጭ የሚያገኙት ብዙሀን ሀገር በቀል ማህበራት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይመዘገቡ እና ህጋዊ ሰውነት እንዳያገኙ ስለሚከለክል፤

- በአንቀጽ 118 (3) መሠረት እነዚህ ሀገር በቀል ድርጅቶች በኤጀንሲው ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውን እንዲነፈጉ ስለሚያደርግ፤

ይህ አንቀጽ ተወግዶ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ማናቸውም ማህበር እና በጎ አድራጎት ድርጅት ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳለው በሚያረጋግጥ አንቀጽ እንዲተካ እንጠይቃለን ፡፡

### 3.3. ለኤጀንሲው የተሰጠው ስልጣን እጅግ ሰፊ እና ለጣልቃ ገብነት በር የሚከፍት መሆኑ

በረቂቅ አዋጁ ለኤጀንሲው የተሰጠው ስልጣን በጣም ሰፊ እና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ተግባራት በእጅጉ ጣልቃ እንዲገባ የሚያደርግ በመሆኑ የመያዶችን ውስጣዊ ነጻነት የሚጥስ እንዲሁም ህልውናቸውን የሚፈታተን ነው:: የኤጀንሲው ኃላፊነት እጅግ ሰፊ መሆኑም ይህንን ለማስፈጸም አቅም አለው ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል:: በተለይ ኤጀንሲው በማህበራት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ምዝገባ፣ ቁጥጥር እና የፈቃድ ስረዛ ሂደቶች የተሰጡት ስልጣኖች ሰፊ እና ጥቅል እንዲሁም ለትርጉም ክፍት በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ በመሆናቸው ተገቢ ላልሆነ አሰራር በር የሚከፍቱ እና ለቁጥጥርም የማያመቹ ናቸው:: ለምሳሌ ምዝገባ የሚለከለከልበትን እና ፈቃድ የሚሰረዝበትን ሁኔታ የሚመለከቱት አንቀጽ 74 እና 105 በምክንያትነት የዘረዘሯቸው እና «በኤጀንሲው ግምት/እምነት» ማህበሩ «የህዝብን ሰላም የሚያደፈርስ ወይም የኢትዮጵያን ደህንነት የሚጎዳ»፣ «የህዝብ/ብሔራዊ ጥቅምን የሚጻረር»፣ «ለግል ጥቅም ይውላል ተብሎ ሲገመት»፣ «ስሙ የማይፈለግ ሲሆን» የሚሉት ሐረጎች ግልጽነት የጎደላቸው እና ለትርጉም እና ተገቢ ላልሆነ አሰራር የተጋለጡ ናቸው:: እነዚህ ሀረጎች የመደራጀት መብትን በማይገድብ እና ለአፈጻጸም በሚመች መልኩ ተለይተው ሊብራሩ እና በዝርዝር ሊቀመጡ ይገባል::

ማህበራትን መሰረዝ/ማፍረስ መሠረታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት የሚመለከት ስለሆነ ተቋማቱን የመሰረዝ/የማፍረስ ስልጣን ሊሰጥ የሚገባው ለኤጀንሲው ሳይሆን ለፍርድ ቤት ነው::

በአንቀጽ 103 እና 104 ለኤጀንሲው የተሰጡት ስልጣኖች ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር ወይም ድርጊት ተፈጽሟል በሚል ጥቅል ምክንያት የማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የስራ መሪዎችና ሰራተኞችን የማገድ፣ የማንሳትና አዲስ ሰራተኞችንና ሃላፊዎችን የመመደብ ስልጣን የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን የውስጥ አስተዳደር ነጻነት የሚጥስ፤ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን የሚያሰፍን እና የመደራጀት መብትንም የሚገድብ ከመሆኑም በላይ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ስልጣናቸውን ያላግባብ እንዲጠቀሙ በር የሚከፍት ነው:: ለኤጀንሲው የተሰጠው ያልተገደበ ጥቅል ስልጣን ለቁጥጥር አስቸጋሪ ስለሚሆን ኤጀንሲው ተጠያቂነት እንዳይኖረው ያደርጋል:: ይህ አንቀጽ በሃይማኖት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ሲሆን ደግሞ ኤጀንሲው የሃይማኖት ተቋማትን መሪዎች ማንሳት፣ ማገድ እና መተካት፣ በስራቸውም ጣልቃ መግባት ይችላል የሚል እንድምታ አለው:: ይህ ደግሞ መሰረታዊ የሆነውን እና በህገመንግስቱ የተቀመጠውን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም የሚለውን መርህ በግልጽ የሚጻረር ይሆናል::

ለኤጀንሲው የተሰጠው ሰፊ የምርመራ ስልጣንም እንዲሁ ኤጀንሲው ባስፈለገው ጊዜ ያለበቂ ምክንያትና ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተቋማቱን እንዲበረብር፣ ኦሪጂናል ሰነዶችን እንዲወስድ፣ ሠራተኞችን እንዲመረምር፣ በስብሰባዎች ላይ መርማሪ/ፖሊስ መኮንን እንዲገኝና እንዲሳተፍ የሚያስችል ስለሆነ የተቋማቱን ነፃነትና የአባላቱን የግለኝነት መብት/right of privacy/ የሚጥስ ሆኖ ይታያል:: በተጨማሪም የምርምራው ሒደት ፍትሐዊ እንዲሆን እና የድርጅቱ እና የሠራተኞቹ የመሰማት እና ራስን የመከላከል መብቶች እንዲጠበቁ /fair hearing and due process of law/ አለመደረጉ ከህገመንግስቱ ጋር የሚቃረን ነው::

ባጠቃላይ ኤጀንሲው የተሰጠው የቁጥጥር ስልጣን ሊቀነስ ይገባል:: የመቆጣጠር እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ስራ በቀዳሚነት በተቋማቱ መዋቅሮችና ውስጣዊ አሰራር እንዲከናወን በሚያስችልና ለኤጀንሲው ክትትል በሚያመች መልኩ አዋጁ ሊሻሻል ይገባዋል:: ኤጀንሲው የሚያደርገው ምርመራ የተመርማሪዎችን ድርጅታዊ ነጻነት፣ የግለኝነት እና ፍትሐዊ የሆነ የመሰማት መብትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል:: የቁጥጥር ስልጣኑም ከተቋማቱ መዋቅሮች አቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር እና ሪፖርቶችን በመመርመርና ችግሮች ሲኖሩ በማጣራት ተገቢውን ክትትል ማድረግ ላይ ሊወሰን ይገባል:: የህጉ መነሻ ተቋማቱ በህጋዊ መንገድ ይሰራሉ የሚል ሆኖ ምርመራ እና የቅጣት ርምጃዎች ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች የሚፈጸሙ /exceptions/ መሆናቸውን ታሳቢ ማድረግ ይገባል::

### 3.4. በረቂቅ ህጉ የተቀመጡት ቅጣቶች በርካታ እና ከባድ ስለመሆናቸው

ረቂቅ ህጉን ወደ ቁጥጥር እና ቅጣት ያደላ ከሚያስመስሉት ነገሮች አንዱ በርካታ /ወደ 26 የሚጠጉ/ የቅጣት ድንጋጌዎችን ማካተቱ ነው:: አብዛኞቹ የቅጣት ድንጋጌዎች አስተዳደራዊ ቅጣት የሚጥሉ

ቢሆንም አስተዳደራዊ ቅጣት ምን እንደሆነ ባለመብራራቱ እና የቅጣቱም አይነትና መጠን አለመታወቁ አዋጁን የበለጠ አስፈሪ እና ግልጽነት የጎደለው አድርጎታል። በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው አስተዳደራዊ ቅጣቶች የሚጣሉት በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ከተቀመጠው ቅጣት በተጨማሪ በመሆኑም አንድ ሰው በአንድ ጥፋት ሁለት ጊዜ አይቀጣም የሚለውን የወንጀል ህግ መርህ የሚጻረር ሆኖ አግኝተነዋል። በተጨማሪም በረቂቁ ኤጀንሲው በድርጅቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በግለሰብ አባላትና ስራ መሪዎች ላይ ቅጣት እንደሚጥል መደንገጉ ኤጀንሲውን ራሱ መርማሪ፣ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ዳኛ እና ራሱ አስፈጻሚ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህም በህገመንግስቱና በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ህጉ ለፍርድ ቤት የተሰጠውን ስልጣን የሚሸረሽር ከመሆኑም በላይ ከመሠረታዊ የስነ ህገመንግስት መርሆዎች ጋር የሚቃረን ነው።

ስለሆነም በአዋጁ ቀላልና ከባድ ጥፋቶች ተለይተው ሊዘረዘሩ እና የቅጣት እርምጃዎችም እንዲሁ ተመጣጣኝ ሆነው በዝርዝር ሊቀመጡ ይገባል። በተጨማሪም በርካታዎቹ ጥፋቶች በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የተሸፈኑ በመሆኑ ወደነዚህ ድንጋጌዎች ብቻ ማመላከቱ ለህጉ በቂ ይሆናል። ከገንዘብ ቅጣቶች ያለፉ ከባድ ቅጣቶችም በፍርድ ቤት ብቻ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል።

### 3.5. **ለሀይማኖት ተቋማትና ልዩ ባህርይ ላላቸው ማህበራት የተለዩ ህጎች ሊወጡ የሚገባ ስለመሆኑ**

በረቂቅ ህጉ የሀይማኖት ድርጅቶች ከሌሎች ማህበራት ጋር በአንድነት መታየታቸው እና በተለይ የፈቃድ ዕድሳትን፣ ቁጥጥርን እና የቅጣት እርምጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በነዚህ ድርጅቶችም ላይ እኩል ተፈጻሚ እንዲሆኑ መደረጉ የሀይማኖት ተቋማትን ልዩ ባህርይና መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም የሚለውን ህገመንግስታዊ ድንጋጌ ያገናዘበ አይመስልም። ስለሆነም የሀይማኖት ተቋማትን ምዝገባ እና አሰራር የሚመለከት ራሱን የቻለ ህግ ቢወጣ የተሻለ ነው። ይህ ህግ የሀይማኖት ድርጅቶች በዓላማ፣በአደረጃጀት እና በውስጥ አሰራር ረገድ ያሏቸውን ልዩ ባህሪያት እና የህገመንግስቱን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ቢሆን መልካም ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ማህበረሰባዊ መሠረት ያላቸው እንደ ዕድር ያሉ ተቋማት ካላቸው አወቃቀር፣ አቅም እና ከሚገኙበት እድገት ደረጃ አንጻር ሲታይ በዚህ ረቂቅ ህግ የተቀመጡትን ዘመናዊ አደረጃጀትና አቅም የሚጠይቁ መስፈርቶች ሊያሟሉ ይችላሉ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም እነዚህ ተቋማት የሚገኙበትን ደረጃ ያገናዘበና የተሻለ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል ሌላ ህግ ቢወጣላቸው የተሻለ ይሆናል ።

### 3.6.**ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ሊፈቀድ የሚገባ ስለመሆኑ**

ኤጀንሲው በምዝገባ፣ በቁጥጥር እና በስረዛ ረገድ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በህገ መንግስቱ እና በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች የተቀመጠውንና መሠረታዊ የሆነውን የመደራጀት መብት የሚነኩ በመሆናቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ተቋማትና ግለሰቦች ለፍርድ ቤት ይግባኝ የሚሉበትን ሁኔታ በህጉ እንዲደነገግ ይጠበቃል። ነገር ግን በረቂቁ አንቀጽ 118 የሚታየው ከዚህ የተለየ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በአንቀጽ 118/1/ እንደተደነገገው ይግባኝ የማለት መብት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ማህበራትና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ብቻ ናቸው። ይህ ድንጋጌ ከአንቀጽ 2/3/ ጋር ሲገናዘብ አብዛኞቹ የሀገር በቀል ድርጅቶች እንደ ውጪ ድርጅት ስለሚቆጠሩ የይግባኝ መብት እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ይህ ደግሞ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 የተረጋገጠውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚገድብ እና በአለም አቀፍ ሰነዶች ጭምር የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት በቂ ህጋዊ ዋስትና እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው። በአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት መሠረት የመደራጀት መብት ሰብዓዊ መብት መሆኑንና በአፈጻጸሙም በዜግነት ላይ የተመሰረተ አድልዎ ሊደረግ እንደማይገባ ታሳቢ ማድረግ ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ በረቂቅ ህጉ ለኢትዮጵያውያን ድርጅቶች የተሰጠው የይግባኝ መብትም ቢሆን በህግ ጥያቄዎች ላይ የተወሰነ ነው። በረቂቁ ላይ ለኤጀንሲው ከተሰጡት ሰፊና ጥቅል ስልጣኖች አንጻር በአብዛኛው የሚነሳው ቅሬታ እና ጥያቄ የአፈጻጸም/የፍሬ ነገር/ እንጂ የህግ አይሆንም። ስለሆነም በፍሬ ነገር ላይ ይግባኝ እንዳይቀርብ መከልከሉ በአንቀፁ የተደነገገውን የይገባኝ መብት ዋጋ የሚያሳጣው ነው። በመሆኑም ህጉ ማንኛውም ማህበርም ሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከኤጀንሲው እና ከዘርፍ አስተዳዳሪው ውሳኔዎች ወደ ሚኒስትሩ ከዚያም ወደ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማለት መብት እንዳለው ሊገለጽ ይገባል።

### 3.7 ከግብር ነጻ ስለመሆንና ስለገቢ ማስገኛ ስራዎች

በረቂቅ ህጉ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ማከናወን ህጋዊ መደረጉ እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከገቢ ግብር ነጻ መደረጋቸው ድርጅቶች አቅማቸውን እንዲገነቡ የሚያስችል ስለሆነ በጣም ጠቃሚ እርምጃ መሆኑን እናምናለን። ለዚህም ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። ይሁንና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ከገቢ ግብር ነጻ ሲደረጉ በልማት እና በዲሞክራሲ ግንባታ ያልተናነሰ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱት ማህበራት ከአባላት መዋጮ ውጭ ባለ ማናቸውም ገቢ ላይ ግብር እንዲከፍሉ መገደዳቸው ፍትሐዊ አይደለም፤ ስለሆነም ይህ ተስተካክሎ ማህበራትም ከገቢ ግብር ነጻ ሊደረጉ ይገባል።

በተጨማሪም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከተጨማሪ እሴት ታክስና ለሥራዎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ገቢ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ላይ የጉምሩክ ታክስ ነፃ ሊደረጉ ይገባል።

ከላይ ያቀረብናቸው አጠቃላይ አስተያየቶች ሲሆኑ በረቂቅ ህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ ያለንን አስተያየት እንደሚከተለው አቅርበናል።